

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከኤፕሪል 21-30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

## ከሜይ 1-10፣11-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2026

አዲስ አበባ


ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

በኤፕሪል ሶስተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች፣ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 39.5፣ 30.6፣ ጎዴ 73.2፣ ጅማ 35.4፣ 33.7፣ ነቀምት 31.9፣ አማን 44.9፣ 32.8፣ ቡርጂ 33፣ ጭራ 51.3፣ ዶሎመና 70.5፣ ሐረር 36.3 ሆሳዕና 31.6፣ ጅግጅጋ 34.2፣ ጅንካ 36.3፣ ካቺሲ 88.4፣ ማጂቴ 35.7፣ ማጂ 39፣ ማሻ 60.2፣ ሳዉላ 42.8፣ 32.7፣ 42.5፣ 42.5፣ ሰኮሩ 30.9፣ ሻምቡ 34፣ ወላይታ ሶዶ 52.7፣ አዳሚቱሉ 38.2፣ አሳሳ 40፣ አታንጎ 37 ቢላምቢሎ 34.6፣ ቡልቂ 30.4፣ ጨለንቆ 40.1፣ 53.7፣ ደብረ ሲና 51.2፣ 45.5፣ ዲመካ 30.3፣ ጊዶሌ 31.8፣ ግራዋ 35.3፣ ጉንዶ በረት 43፣ ሀገረ ሰላም 46.8፣ ሃሮ 40፣ ሃርሺን 38.3፣ ቀርሳ-ሶማሌ 40.4፣ ቅዳሜ ገበያ 36.6፣ 48.7፣መቂ 30.6፣ ናቲራ 30.6፣ ኦንጋ 45.7፣ ሰቆታ 48፣ 30፣ ሺንዲ 33.5፣ ይርጋ ጨፌ 57.8፣ እንዲሁምይርጋለም 48.8፣ ዶጋ 36.5 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በሃምሳ (50) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡





ምስል1: ከኤፕሪል 21 እስከ 30 /2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በልግ ዋነኛ እና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ ኤረር፣ ሸበሌ፣ ዶሎ፣ ኖጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ እና ሊበነ ዞኖቸ፣ ከአማር ክልል የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግህብራ፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ ዞኖች ላይ ከ81-181 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ ኤረር፣ ሸበሌ፣ ዶሎ፣ ኖጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ እና ሊበነ ዞኖቸ፣ ከአማር ክልል የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግህብራ፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ የሰሜንና መካከለኛዉ ጎንደር፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃላባ፣ ሃዲያና ከንባታ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ34.0-41.5 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል (ምስል 2) ።








ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30 /2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30 /2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30 /2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር




ምስል፡2 ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ34 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

1.2


## 1.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የኤፕሪል ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ ምሥራቅና በምዕራብ የሀገሪቱ የበልግና የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ቀደም ብለው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች እድገት የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች ዘር ለመዝራትና ቀደም ብለው ለተዘሩ የመኸር ሰብሎች እድገትና ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲሁም ለእርሻ ስራ የጎላ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን  በአንፃሩ ግን በደቡብ ምእራብ ክልል በወይታ ዞን በዳሞ ጋሌ ወረዳ የነበረው ከባድ መጠን ያለው እርጥበት የመሬት መንሸራተት በማስከተሉ በሰው ህይወት፣ ንብረትና በሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)።


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሶስተኛ አሥር ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ኦጋዴን፣ የመካከለኛውና የላይኛው ተከዜና የአባይ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። በተጨማሪም በአብዛኛው የላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜና በላይኛውና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እስከ መጠነኛ የሚደርስ የገፀ ምድር ውኃ ፍሰት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የገጸምድር፣ የከርሰምድር እንዲሁም ለመስኖና ለሃይል ማመንጫና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በአንጻሩ ግን በጎዴ አካባቢ ከጣለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተፈጠር ጎርፍ በንብረትና በመሰረተ ልማት ላይ መጠነኛ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

ሜይ የበልግ ወቅት የመጨረሻ ወር ሲሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ዝናቡ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ በመሄድ ብዙ ቦታዎችን ይሸፍናል፡፡ በዚህም መሠረት አብዛኛው የኦሮሚያ ክልልን ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ የሲዳማ ክልል፣የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ121-260 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-20 ቀናት ያህል ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይና የአማራ ምዕራባዊ ክፍልና የሱማሌ አካባቢዎች ከ41 እስከ 120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ለ10 ቀናት ያህል በአማካይ ያገኛሉ። ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በሜይ የመካከለኛው፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

### 2.1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በሜይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን በማቋረጥ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ ደብብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute


በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ምስራቅ፣ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡

በተጨማሪም በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡


በሌላ በኩል በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በሜይ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ32 እስከ 39.6 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10 /2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10 /2026, የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

Ethiopian Meteorology Institute


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ነጎብ፣ ቆራሂ፣ ጃረር፣ ዶሎ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | |
| አሮሚያ | ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወላጋ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ድቡበ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| አፋር | ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ሀዉሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ፣ ኤረር እና ፋፈን ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11-30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |




ምስል 6፡ ከሜይ 1-10, በ24 ሰዓት ውስጥ ከሰላሳ ስድስት (36) ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ የሚመዘገብባቸዉ

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 2.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 21/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የሜይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሜይ የሁለተኛዉ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና፤ በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡባዊው አጋማሽ፤ በመካከለኛው እና በምስራቅ  የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው የበልግ ሰብል አብቃይና ተጠቃሚ እንዲሁም የመኸር እርሻ ስራ ቀድመው ለሚጀምሩ በተለይም የደቡብ፤ የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የምስራቅና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በመሆኑም ከሚጠበቀው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና የሚጠበቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

## 2.4 እ.አ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው የገጸምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በመሆኑም ከሚጠበቀው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና የሚጠበቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የመኸር እርሻ ስራ ቀድመው የሚጀምሩና የበልግ ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ፣ ሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወላጋ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሲቲ፣ ኤረር እና ፋፈን ዞኖች | ➢ ግብርና ስራ በቂ የአፈር እርጥበት መኖር<br>➢ ፍሬ በማፍራትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት<br>➢ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት<br>➢ በቂ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መኖር<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሀ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት | ➢ የአፈር መሸርሸር<br>➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት<br>➢ የሰብል ማሳ ላይ ውሃ የመተኛት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት፤<br>➢ የአረም መከሰት<br>➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር | ➢ የውሃ ማፋሰሻና ማንጣፈፊያ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>➢ የአፈርና የውሃ እቀባ ስራዎችን መስራት፤<br>➢ የሰብል ማሳዎችን ክትትል ማጠናከር<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን እንዳይከሰት አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የጎርፍ መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የአየር ጠባይ ትንበያንና ምክረሃሳቦችን መከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፤ |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ዳዋ፣ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ነጎብ፣ ቆራሂ፣ ጃረር፣ ዶሎ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግህምራ፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌርና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ሀውሲ፣ ማሂ፣ ሃሪና ጋቢ ዞኖች፣ ሲቲ፣ ኤረር እና ፋፈን ዞኖች ፣ የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ➢ ለመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹነት<br>➢ ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለተለያዩ የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ | ➢ ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት መኖር፤<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤ | ➢ የመኸር ሰብሎች ጊዜውን ጠብቆ መዝራት<br>➢ የዝናብ ውሃን የመሰብሰብና የማጠራቀም<br>➢ የአፈር ትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ የአፈር እቀባ ስራ ማከናወን፤<br>➢ የእንስሳት ግጦሽ ሣር በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከባድ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ በላይኛውና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋና ዋቢ ሸበሌ፣ | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ የውሃ ይዘት መጨመር<br>• ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>• የኩሬና የወንዝ የውሃ መጠን መጨመር | • ቅጽበታዊ ጎርፍ መፈጠር<br>• የከተሞች የዉሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፍ ቅድመ መከላከል ስራዎች መስራት<br>• የዝናብ ውሃን ማሰባሰብ እና ማከማቸት<br>• የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ማጽዳት |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በአብዛኛው አዋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ እንዲሁም ተከዜ | • መጠነኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት መሻሻል | • አንጻራዊ የትነት መጨመር<br>• የደረቅ ሰሞናት በመብዛት | • የዉሃ ብክለት መቀነስ<br>• የሚገኘውን መጠነኛ ዉሃ በአግባቡ መያዝ<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በመጠቀም የጊዜ ተመን እቅድ ማዘጋጀት |
| **በደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በአብዛኛው አፋር ደናክል በታችኛው ገናሌ ዳዋና ዋቢ ሸበሌ | | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • ዉሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• የውሃ መቆጠብያ ዘዴዎችን መተግበር<br>• የውኃ ማከማቻ (water harvesting) መርህ ግብሮች ማጠናከር |